# የትራንስፖርት አገልግሎትን የተመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎች

## ተማሪዎን ከ 2019-20 የትምህርት ዓመት ማዘጋጀት




የ 2018-19 የትምህርት አመት እየተገባደደ ሲመጣ፣ የ Denver Public Schools (DPS) የትራንስፖርት አገልግሎቶች ለዚህ የተሳካ አመት ሊያመሰግናችሁ ይወዳል። የ DPS ትራንስፖርት አገልግሎት ለሁሉም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እኩል እድል በማመቻቸት እና የወላጆችን ፍላጎት በማሟላት ለአካዳሚያዊ ስኬት የመግቢያ በር ነው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሰፈረውን ለቀጣዩ የትምህርት አመት ለመዘጋጀት የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮችን የያዘውን መረጃ ይከልሱ።

## የአዲስ የትምህርት ዓመት እርምጃዎች

### ቤተሰብዎ ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን ከመዘጋጀት የሚረዳቸው ጠቃሚ እርምጃዎች

### ☑ የአውቂያ መረጃዎ ወቅታዊ መሆኑን ያረጋግጡ

ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ከመኖሪያ አድራሻቸው የመውሰድና የመመለስ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ስለሚሰጡ ትምህርት ቤት ለሚማር እያንዳንዱ ተማሪ ትክክለኛ አድራሻ መያዝዎ በጣም አስፈላጊ ነው። የአድራሻ ለውጦች የሚከወኑት በተመደቡበት ትምህርት ቤት የፊትለፊት ቢሮ ብቻ ነው።

### ☑ የአውቶቡስ መረጃን ለማግኘት የወላጅ ፖርታል/የትራንስፖርት ድህረገፅን ይመልከቱ

በ Success Express አውቶቡሶች ለማይጓዙ ተማሪዎች፣ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የአውቶቡስ የጉዞ መስመር መረጃ ከጁላይ መጨረሻ/ኦገስት መጀመሪያ ጀምሮ በወላጅ ፖርታል ላይ ባለው የትራንስፖርት ገጽ ላይ የሚገለጽ ይሆናል። በ Success Express አውቶብሶች ለሚጓዙ ተማሪዎች፣ መርሃ ግብሮቹ በጁላይ መጨረሻ/ኦገስት መጀመሪያ ላይ በ transportation.dpsk12.or ላይ የሚገለጹ ይሆናል። መረጃው ሊለወጥ ስለሚችል የአውቶቡስ መረጃን ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በፊት ብዙ ጊዜ እንዲያረጋግጡ እንመክራለን።

### ☑ አስፈላጊ ከሆነ የመስመር ላይ የልዩ ሁኔታ መጠየቂያ ቅጽን ይሙሉ

በወላጅ ፖርታል ውስጥ የአውቶቡስ መረጃ ከሌለ እና ተማሪዎ ለ Success Express አውቶቡሶች ብቁ ካልሆነ፣ ልጅዎ ለትራንስፖርት ብቁ ላይሆን ይችላል። በፖርታሉ አማካኝነት የመስመር ላይ የትራንስፖርት ልዩ ሁኔታ መጠየቂያ ቅጽን መሙላት ይችላሉ። ለ 2019-20 የትምህርት ዓመት የሚቀርቡ የትራንስፖርት የልዩ ሁኔታ ጥያቄዎች ከሰኞ፣ ጁላይ 15 እስከ አርብ፣ ጁላይ 26 ድረስ ሊቀርቡ ይችላሉ። የሚወሰዱ ውሳኔዎች ዓርብ፣ ኦገስት 16 ላይ ይገለፃሉ። በልዩ ሁኔታ ጥያቄዎች ላይ የተላለፉ ውሳኔዎች በሙሉ በኢሜል ለላኪው ኢሜል ይላካሉ።

### ☑ አዲስ ወይም ምትክ +Pass ማግኘት

አዲስ ወይም ምትክ +Pass ከተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ቢሮ ጸሐፊ መጠየቅ አለበት። ከዚያም ቋሚ + Pass እስኪዘጋጅ እና እስኪታተም ድረስ፣ ጸሃፊዋ ለተወሰነ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ጊዜያዊ + Pass ለተማሪው/ዋ ይሰጣሉ። ቤተሰቦችም በኦገስት ወር መጀመሪያ ላይ ወደ ትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተዳደር ሕንፃ በመምጣት አንድ የ + Pass ማግኘት ይችላሉ። ሰዓት፦ ከ 8 a.m.-12 p.m.፤ ከ 1-4 p.m. | ቦታ፡ 2909 W 7th Ave., Denver 80204. ያስታውሱ፦ በ **2018-19 የትምህርት ዘመን የተከፋፈሉ የ +Pass ካርዶች ለ 2019-20 የትምህርት ዘመን መስራታቸውን ይቀጥላሉ።**

### ☑ ከእኛ ጋር ይገናኙ

Transportation.dpsk12.org በእነዚህ ሁሉ ዙሪያ ዝርዝር መረጃ ያለው ሲሆን ለመነሻ ያህልም ጥሩ ነው። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ በ transportation@dpsk12.org ላይ በኢሜል ወይም ከሰኞ እስከ አርብ ድረስ በመደበኛ የስራ ሰዓታት በ 720-423-4699 ላይ ለስምሪት አገልግሎቶች ቡድን ይደውሉ።



1819_EOY_Mailer_Parents_Amharic.indd 1 5/13/2019 3:12:03 PM

# የ Bus Bulletin

የ 2019-20 የትምህርት ዓመት አስታዋሾች

በት/ቤት አውቶቡስ የሚጓዝ ተማሪ ካለዎት የ DPS ትራንስፖርት አገልግሎት ዲስትሪክቱ ስለ ተማሪዎ የተማሪ አውቶቡስ አገልግሎት ቅጽበታዊ እና ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያሳውቅ የሚያስችለውን የአውቶቡስ ቡሊቲን (ማሳወቂያ) ያቀርባል። በአደጋ፣ በሜካኒካዊ ወይም በአየር ሁኔታ ምክንያት አውቶቡሶች ከ 10 ደቂቃ በላይ ዘግይተው ሲመጡ በጽሑፍ መልእክት፣ በኢሜል እና/ወይም በድምፅ ማሳወቂያዎች የቤተሰብ አባላት እንዲያውቁት ይደረጋል።

ለትራንስፖርት አገልግሎት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የቤተሰብ አባላት ለትምህርት ቤት ሲመዘገቡ በሰጡት የስልክ እና የኢሜይል አድራሻ መሰረት በሁለቱም ከአውቶቢስ ቡሊቲን በሚላኩ የድምፅ መልእክት እና የኢሜይል ማሳወቂያዎች በቀጥታ ይመዘገባሉ። ቤተሰቦች በጣም የቅርብ ጊዜው የመገኛ መረጃቸው በአውቶቡስ ቡሊቲን መካተቱን ለማረጋገጥ/ለማሻሻል ወደ ወላጅ ፖርታሉ እንዲገቡ ይበረታታሉ።

## የትራንስፖርት አገልግሎቶች ድረገጽ፡-

*የትራንስፖርት አገልግሎቶች ለቤተሰቦች እና ተማሪዎችን ጠቃሚ የመጓጓዣ መረጃ ለማቅረብ transportation.dpsk12.org ን ለማሻሻል በ 2018-19 የትምህርት ዓመት በሙሉ በትጋት ሰርቷል። ቤተሰቦች በአገልግሎቶቻችን ላይ ግብረመልስ ማስገባት፣ እንዲሁም የጠፉ እቃዎች ማረጋገጫ ጥያቄ ማስገባት ይችላሉ። ስለ ምናቀርባቸው አገልግሎቶች መረጃን ለማግኘት ሁሉም የትራንስፖርት ድር ጣቢያን እንዲጎበኙ እና በማንኛውም ለውጦች ላይ ወቅታዊ መረጃ እንዲይዙ እናበረታታለን።*




# የልዩ ፍላጎት ትምህርት ትራንስፖርት

### ለመጀመሪያው የትምህርት ቀን ለመዘጋጀት እንዲረዳዎ ጠቃሚ መረጃ

ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ለተለዩ ተማሪዎች፣ የ Individualized Education Program (IEP፣ የግለሰባዊ የትምህርት መርሃ ግብር) ምደባ ልጅዎ መጓጓዣ እንደሚያስፈልገው ይወስናል። የትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተማማኝ ትራንስፖርትን ለማረጋገጥ የተማሪዎን ልዩ ፍላጎቶች በተመለከተ ከ Office of Student Equity and Opportunity (የተማሪ እኩልነት/ፍትሃዊነት እና ዕድል ቢሮ) ሙሉ እና ትክክለኛ መረጃ መቀበል አለባቸው። የትራንስፖርት አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የትራንስፖርት የመረጃ ቅጽ ያስፈልጋል። በ Family Education Rights and Privacy Act (FERPA፣ የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ሕግ) መሠረት፣ የተማሪዎች ግላዊ መረጃ በሙሉ በጥብቅ ምስጢራዊ ነው።

## ስለ ሂደቱ

የግለሰባዊ የትምህርት እቅዳቸው (IEP) ትራንስፖርትን እንደ ተዛማጅ አገልግሎት የሚይዝ ልዩ ፍላጎቶች ያላቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች፣ ሂደቱን የተማሪያቸውን የልዩ ፍላጎት መምህር በማናገር መጀመር ይኖርባቸዋል። በመስመር ላይ የ 1066 ቅጽ በተማሪው አስተማሪ ወይም የት/ቤት ተወካይ መጠናቀቅ እና ለ DPS Student Equity and Opportunity (SE&O፣ የተማሪ እኩልነት/ፍትሃዊነት እና ዕድል ቢሮ) ገቢ መደረግ አለበት። ፎርሙ ከደረሰ በኋላ፣ የ SE&O የድጋፍ አጋር ትራንስፖርትን በቀጥታ ከ DPS የትራንስፖርት አገልግሎቶች ጋር ያስተባብራል።

## የትራንስፖርት ጥያቄዎችን የማካሄጃ የጊዜ ሰሌዳ

አንዴ የ SE&O የድጋፍ አጋር ጥያቄውን ወደ ትራንስፖርት አገልግሎቶች ካቀረበ በኋላ፣ ጥያቄውን ለማካሄድ እስከ 10 የሥራ ቀናት ሊወስድ ይችላል። የአድራሻ እና የእውቂያ መረጃ ወቅታዊ ካልሆነ ይህ የጊዜ ሰሌዳ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ የትራንስፖርት መጓተት መቀነስን ለማገዝ፣ ልዩ ፍላጎቶች ያላቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች መረጃው ወቅታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጋው ወራት ውስጥ የማሳወቂያ አስታዋሾች ይደርሳቸዋል።

## ለጥያቄዎች ማን ሊያነጋግሩ ይችላሉ

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ትራንስፖርት አቅርቦትና አያያዝን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በሙሉ በልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር በኩል ለ SE&O ድጋፍ አጋር መሰጠት አለባቸው። ቤተሰቦች በአሽከርካሪ ላይ (transportation@dpsk12.org) ግብረመልስ ለማስገባት፣ ወይም የተማሪን መቅረት ሪፖርት ለማድረግ ብቻ በቀጥታ ከትራንስፖርት አገልግሎቶች ጋር መገናኘት አለባቸው።

የተማሪ መቅረቶችን ሪፖርት ማድረግ፡

- በቢጫ አውቶቡስ የሚጓዙ ተማሪዎች፡ 720-423-4624 DPS ሬዲዮ ስምሪት
- American Logistics Company (የአሜሪካን ሎጂስቲክስ ኩባንያን) የሚጠቀሙ ተማሪዎች 855-292-4364፣ አማራጭ 1

ስለዚህ ሂደት ተጨማሪ መረጃ በ transportation.dpsk12.org/eligibility-and-routing/special-education-services/ ላይ ማግኘት ይቻላል።



1819_EOY_Mailer_Parents_Amharic.indd 2 5/13/2019 3:12:09 PM